የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፣

# ዜና ።

መጀመሪያ ቊጥር ፣

በመንፈሳዊ ጉባኤ ዋና ጽሕፈት ቤት ፣
ተጠባባቂነት ታተመ ።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፣
አዲስ አበባ ኅዳር ፲ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ማ ው ጫ ።


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| | መጀመሪያ ክፍል ። | |
| ፩ ፤ | ከታሪኩ ባጭሩ . . . . . . | ፯ |
| ፪ ፤ | የተቀደሰው ዓቢይ መንፈሳዊ ጉባዔ ሥራውን ሲጀምር ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የተናገሩት ቃል ። | ፱ |
| | ሁለተኛ ክፍል ። | |
| ፫ ፤ | ከታሪኩ ባጭሩ ። . . . . . . | ፲፭ |
| ፬ ፤ | በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ጉዳይ ባ፲፱፻፴፮ ዓ. ም. በሰኔ ፲፪ና ፲፫ አዲስ አበባ ላይ የተደረጉ ንግግሮች ። | ፲፯ |
| ፭ ፤ | ከኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባዔ ባ፲፬ ሰኔ ፲፱፻፴፮ ዓ. ም. ተጽፎ ለብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የተላከ ፤ ፯ ጥያቄዎች የተመለከቱበት ደብዳቤ ። . . | ፳፰ |
| ፮ ፤ | ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ከጥያቄው አንዳንዱን በመቃወም በየካቲት ፳፪ ቀን/ ፴፯ (1. 3. 45) የጻፉት ደብዳቤ ። . . . . . . | ፴፩ |
| ፯ ፤ | ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በመጋቢት ፲፱ / ፴፯ ለብፁዕ የእስክንድርያ ፓትረያርክ የጻፉት ደብዳቤ ። | ፴፬ |
| ፰ ፤ | የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ስለ መልሱ ለአቡነ መቃርዮስ በመጋቢት ፲፰ / ፴፯ የጻፈው ደብዳቤ ። | ፴፭ |
| ፱ ፤ | የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄዎች ዋነኞቹን ጉዳዮች አለመቀበሉን ያስረዳበት በ፱ ሰኔ ፲፱፻፴፯ የተጻፈ ። | ፴፰ |
| ፲ ፤ | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ ከኮፕትጉባኤ በ፱ ሰኔ ፲፱፻፴፯ የተጻፈለትን ደብዳቤ ተመልክቶ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ያቀረበው የውሳኔ ማስታወቂያ ። . . . . | ፵፬ |


www.ethiopianorthodox.org

## መጀመሪያ ክፍል ።

## የተቀደሰ ዓቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ።

## በኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. ሥራውን ስለ መጀመሩ ።

. ፩ .

### ከታሪኩ በጭሩ ።

ከያውራጃው በአብያተ ክርስቲያኖች ተመርጠው የመጡ መል እክተኞች ፣ ሊቃውንትና የታላላቅ ገዳማት መምህራን የተሰበሰቡ በት የተቀደሰ ዓቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ በኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. እሑድ በ፱ ሰዓት ሥራውን ሲጀምር የቤተ መንግሥት መልከተ ኞች የሆኑ መኳንንት የቤተ መንግሥቱን አሳብ ለማስረዳት ከዚ ያው ነበሩ ። ሊቃውንቱ መጀመሪያ ጸሎተ ማኅበር አድርሰው ልመ ናቸውን ወደ እግዚአብሔር አቀረቡ ። ከጸሎት በኋላ የጉባኤው አለቃ ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የሥራውን አጀማመር የሚ ያስረዳ ንግግር አደረጉላቸው ። የብፁዕነታቸውም ንግግር ወደፊት ተጽፎ የሚገኘው ነው ።
(ገጽ ፱ ተመልከት)

ከብፁዕነታቸው ንግግር በኋላ ሊቃውንቱ በየማዕርጋቸው ሲቀ መጡ የያንዳንዱ አገር መልክተኛ አሳቡን ባጭር ቃል መግለጽ ጀመረ ። «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን መቻል ይገባታል» የሚለው ድምፅ በሚያስደንቅ ኅብረት አዳራሹን ሞላው ።

ከቤተ መንግሥት መልክተኞች መካከል ፣ ክቡር አፈ መስፍን እንዳርጋቸው መሰይ በቤተ መንግሥት በኩል ያለውን አስተያየት ሲያመለክቱ እንዲህ አሉ "የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ከኢትዮጵያ መንፈሳውያን አባቶች መካከል በዚሁ ጉባኤ ተመርጦ በእስክን ድርያው ፓትርያርክ እንዲሾም ፣ ቤተ መንግሥት መልክተኞች ልክ እንደ ገና የመጨረሻ ቃል ይቀበላቸው ዘንድ ያስፈልግ ይመስለ ኛል ። እነሱ ገፍተው እስኪጥሉት ድረስ ከቤተ ክህነት የተጀመ ረውን የትሕትና ጥያቄ ፣ ቤተ መንግሥት ደግሞ በበኩሉ ሊደክ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ምበት የሚገባ ነው ። በዚያውም ላይ ትሕትናችንና ትዕግሥታችን ዓለም እስኪያውቀው ድረስ ሆኖ ቢገለጽ ያስመሰግናል እንጂ ልናደርገው የሚገባንን አሳብ ከመፈጸም አያግደንም እክ እያሉ በሰፊው አስረዱ ።

የአብያተ ክርስቲያናት መልክተኞችም መልሱን ሲሰጡ እንዲህ አሉ « እስከ ዛሬ ድረስ በየጊዜው የተላከው ጥያቄ ለትሕትናችንና ለትዕግሥታችን በቂ ማስረጃ ነውና አሁን ሥራችንን መፈጸም ብቻ ይገባናል ። ነጻነት ያለው ያንድ መንግሥት ሕዝብ በቤተ ክርስቲያኑ በኩል ያለፈቃዱ በግድ ለሌላ ዜጋ ተገዥ ሆኖ መኖር አይቻለውም ። እኛ መልክተኞች ሆነን የመጣንላቸው አገሮች ካህናቱም ምእመናኑም ያስገነዘቡን ሥራችንን እንድንፈጽም ነው አሉ ።

ከብዙ ንግግር በኋላ ማንኛውንም አሳብ እንደገና ለማጥናትና ወደፊት ንግግሩን ለመቀጠል ቀጠሮ ተደርጎ ጉባኤው ተመለሰ ።

---



## የተቀደሰው ዓቢይ መንፈሳዊ ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ፤ የተናገሩት ቃል ።

የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች ።

ሊቃውንትና መምህራን ሆይ ።

ዛሬ የተሰበሰብንበት ጉዳይ ያገራችን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊ ማዕርግ በዓለም እንዳሉት እንደ ክርስቲያን አገሮች የሚገባትን ክብር አግኝታ የምትኖርበትን ቁርጠኛ አሳብ ለመወሰንና ለመመሥረት ነው ።

ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ድረስ በሥርዓተ ኦሪት ስትኖር የነበረችው የኛ ቤተ ክርስቲያን ፤ የክርስትናን ሥርዓት ለመቀበል የበቃችው ነገሥታትዋ ፈቅደው በላኩት በፍሬ ምናጦስ መልክተኛነት ነው እንጂ ከዚያ በፊት ከግብጽ ፤ ወይም ከሌላ ስፍራ ወደ አክሱም መጥቶ የሰበከ እንዳልነበረ ታሪኩ በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነውና ዝርዝር ሐተታ የሚያስፈልገው አይደለም ፤ ስለዚህም ኢትዮጵያ ክርስቲያንነትን በፈቃድዋና በትጋቷ ብቻ ከማግኘቷ በቀር እኔ መሥራች ነኝ ብሎ የሚመካበት የለም ።

ፍሬ ምናጦስ ላገራችን መጀመሪያ ጳጳስ ተብሎ በነገሥታቱ ጥያቄ ተሾሞ ከመጣ ወዲህ ፤ ጳጳስ ሲሞት ከእስክንድርያ ሌላ ጳጳስ አሹሞ ማስመጣት ልማድ ሆነ ። ይህ አኳኋን አዲስ ተክል በሚያሰኝበት በመጀመሪያው ሰዓት ምናልባት አስፈላጊ ሆኖ ኖሮ ይሆናል ። ቤተ ክርስቲያን በትምህርትም ፤ በስብከትም ራሷን ከቻለች በኋላ ግን አስተዳዳሪዋን ከራስዋ ለማግኘት ፈላጊ ሆነች ።

በታሪክ እንደምናውቀው የመጀመሪያው ክርክር ባ፲፩ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነገሡው በአጼ ይምርሃ ዘመን ተደረገ ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ለመቻል መንቃትዋ ከታወቀ በኋላ ፤ «የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቆቻቸው ውስጥ አለቃ የሚሆናቸውን አባት አይሹሙ› የሚል ቃል ፤ በቅዱሳን አበው በሠ

www.ethiopianorthodox.org

ለስቱ ምዕት ስም አመከኘተውና በኒቅያ ጉባኤ እንደ ተደረገ አስ መስለው ፤ የተገኘርነት ፡ ሥርዓት በኢትዮጵያ ብቻ ጻፉበት ። ባለ ፈው ዘመን የግብጽ መልክተኞች እንዳስታወቁን በዓረብኛው የተ ጻፈውማ ፤ «አዋቆቻቸውን አይሹሙ እነሱም ራሳቸው አይሾሙ » የሚል ስለ ሆነ በግዕዙ መጽሐፋችን የተጻፈውን እንኳ አሁን አፉ ልሰውታል ።

በኢትዮጵያውያን ላይ የተጻፈብን ይህ ቃል ከአባቶቻችን ከሠ ለስቱ ምዕት ሳይሆን ከባለጥቅሞች በኋላ ዘመን የተፈጠረና የተ ጨመረ መሆኑ የታወቀው ፤ በኒቅያ ጉባኤ የነበሩትና መጽሐፉን የያዙት ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ፤ ለምሳሌ ፤ ቊስጥንጥንያ ፤ አን ጾኪያ ፤ ሮምያ ይህን ነገር በጭራሽ እንደማያውቁትና በመጽሐፋ ቸው አለመኖሩ ስለ ታወቀ ነው ።

እንዲያውም ቢሆን ነገሩን ለሚመረምር ከዚህ ቀጥሎ የተ ጻፈው ቃል የሚያስረዳ ነው ። የኒቅያ ጉባኤ የተደረገው በ፫፻፳፭ ዓ ፡ ም ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ሥርዓተ ክርስትናን የተቀበለችው ግን ከኒቅያ ጉባኤ በኋላ ፫ ዓመት ቆይታ (ሌሎች ባለታሪኮች እንደሚሉ ትም ቢሆን ፲፫ ዓመት ቆይታ) ስለ ሆነ ፤ ከማመንዋና ሥርዓተ ክርስት ናን ከመቀበሏ በፊት ይህ ትእዛዝ ታወጀባት ሊባል የማይቻል ነው ።

የሆነ ሆኖ ይህ የጵጵስና ሹመት በየጊዜው ክርክር ሲደረግበትና አንድ ጊዜ ፍጻሜ ሲያገኝ አንዳንድ ጊዜም ሲሰናከል የኖረ ነገር ነው ። በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ዋና ሐዋርያ የነበሩት አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያውያን የሊቃውንት ጉባኤ (ሲኖዶስ) ተመርጠው ጳጳስ ሆነዋል ። ከሳቸው በኋላም በመንበራቸው የተተኩት ፫ኛው ዕጨጌ አቡነ ፊልጶስ ጳጳስ ሆነው ነበር ። በአፄ እስክንድርም ዘመን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሊቀ ጵጵስና የሚከ ለከሉት በምን መርገም ነው ? የሚል ታላቅ ክርክር ተነሥቶ ነበር ። ከዚያም በኋላ በየጊዜውና በየዘመኑ የተደረገውን ማሰብ የተገባ ነገር ነው ።

በልማድ ከአንድ አገር ጳጳስ ማስመጣት በኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም አገሮች ላይ ነበረ ። ነገር ግን ልማዱ በልማድ ታድሶ እነሆ ሁሉም ነፃነቱን አግኝቷል ። ለምሳሌ የአንጾኪያ ቤተ ክርስ



ቲያን የቆጵሮስንና የጆርጂያን ቤተ ክርስቲያን ታገዝዝ ነበር ። አሁን ግን ሁለቱም ራሳቸውን ችለዋል ። እንዲሁ ደግሞ የቊስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን የአቴናንና የመስኮብን ፤ የሴርብያንና የሩማኒያን ቤተ ክርስቲያኖች ታገዝዝ ነበር ። አሁን ግን ሁሉም ራሳቸውን ችለው በክርስቶስ እምነት ጐልምሰዋል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያንም የጠየቀችው ተወላጅዋ ማዕርገ ሢመት እንዲያገኝ ነው እንጂ ከአንድነት ለመለየት ስላልሆነ የነገሩ አኳኋን በሌሎቹ አብ ያተ ክርስቲያናት ከተደረገው ጋራ ሲነጻጸር በጣም የለሰለሰ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የዛሬ ፲፯ ዓመት ስለ መብትዋ የጠነከረ ጥያቄ አቅርባ ነበር ። ከብዙ ንግግር በኋላም በንጉሠ ነገሥታችን ትጋት አምስት ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲሾሙ ሆኖ ተቈረጠ ። እነርሱም በፓትርያርኩ በአቡነ ዮሐንስ ተባርከው በግንቦት ፲፰ ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. ካይሮ ላይ የተሾሙት አራቱ ጳጳሳትና በጥር ፩ ፲፱፻፳፬ ዓ. ም. አዲስ አበባ የተሾሙት አም ስተኛው ጳጳስ ናቸው ። እነዚህንም አምስቱን ጳጳሳት መርጦ ያቀ ረባቸው በ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. በመስከረም ፬ ቀን የተመሠረተውና አሁንም ያለው የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው ።

በጠላት ወረራ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ደረሱባት ። ፩ኛ/ ጳጳሳቱ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል ተገደሉ ። አብያተ ክርስቲያናቱ ተቃጠሉ ፤ መምህራኑ ተደበደቡ ፤ እንደ እነ ደብረ ሊባኖስ ያሉት ታላላቆቹ ገዳማት ተመ ዘበሩ ። መነኰሳቱም ተገደሉ ። ፪ኛ/ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ስለ ጕዳ ያቸው ባደረጉት ጥያቄ መሠረት ወደ ሮማ ሄደው ነበርና ከዚያ ሲመለሱ ባገራቸው ቀሩ ። ፫ኛ/ ለምክሩም ሆነ ለመረዳዳቱ ወደ አባቶቻችን ወደ ግብጻውያን የሚያደርሰው መገናኛው ሁሉ በጠላት የጦር ኃይል እጅ የተጠበቀ ነበር ።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቃውንቱንና መም ህራኑን ምእመናኑን ጭምር ሰብስቦ ጉባኤ (ሲኖዶስ) አቁሞ የጎ ንደርና የጎጃም ጳጳስ የነበሩትን አቡነ አብርሃምን ለሊቀ ጵጵ ስና መረጣቸውና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚሁ መሠረት

www.ethiopianorthodox.org

የምትተዳደር ሆነች ። ይኸውም ነገር ግብጻውያን ደስ ያልተሰኙበትና ችግራችንን ሳይመለከቱ ግዝት እስከ ማድረግ የደረሱበት ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያን ነፃነት ይዘው ከተመለሱ በኋላ የመጀመሪያዎቹ ፲ ወሮች ፣ ፈርሶ የነበረውን መንግሥት እንደ ገና በማቋቋም ያለፉ ናቸው ። ባ፲፱፻፴፬ ዓ ም በመጋቢት መጨረሻ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ንግግር ተጀመረ ። ወዲያው የግብጽ ፓትርያርክ መልክተኞች ከጳጳሱ ከአቡነ ቄርሎስና ከቤተ መንግሥቱ ሹማምንት ጋር ወደ አዲስ አበባ መጥተው በሰኔ ወር ንግግር ተደረገ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበችው አሳብ ለግብጽ መልክተኞች ባ፲፭ ሰኔ ተሰጥቷቸው ሲሄዱ ገና ከመድረሳቸው በፊት ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ በድንገት ማረፋቸው ባ፲፰ ሰኔ ተሰማ። በመንበራቸውም የሚተኩት አዲሱ ፓትርያርክ እስኪመረጡና እስኪሾሙ ድረስ ፲፱ ወሮች ያህል ስለ ፈጀ ነገሩ ፍጻሜ ሳያገኝ ዘገየ ።

አቡነ መቃርዮስ ባ፲፱፻፴፯ ዓ ም በየካቲት መጀመሪያ ከተሾሙ በኋላ ንግግሩን ለመቀጠል የግብጽ መልክተኞች በግንቦት ወር ወደ አዲስ አበባ መጡ ። እነዚህ መልክተኞች ስለ ፊተኛው ጥያቄ መልሱን ይዘው ይሆናል ተብለው ሲጠበቁ አንዳች መልስ አለመያዛቸውንና ለንግግር የመጡ መሆናቸውን አስረዱ ። ከብዙ ንግግር በኋላም የኢትዮጵያ ሊቃውንት መክረው ያቀረቡት አሳብ በ፳፩ ሰኔ ተሰጥቷቸው ተመለሱ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበችው ጥያቄ ፍሬ ነገሩ ከዚህ በታች በተመለከቱት በ፯ ክፍሎች የተገለጸ ነው ።

፩ኛ ፤ ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ በቤተ ክህነት ክፍል አድገው በሃይማኖት ጸንተው ከሚኖሩት ከመንፈሳውያን አባቶች ለሊቀጳጳስነት የሚገባው ሰው ተመርጦ ፤ በእስክንድርያው አባታችን ተባርኮና ተቀብቶ እንዲሾምላት ፤

፪ኛ ፤ የእስክንድርያው ሲኖዶስ በሚመረጥበት መሠረት የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ለጵጵስናና ለኤጲስ ቆጶስነት የሚገቡትን መንፈሳውያን አባቶች እንዲመረጥና ከእስክንድርያ አባታችን ተቀብቶ የመጣው ሊቀ ጳጳስ ባርኮ እንዲሾማቸው ፤



፫ኛ ፤ በማርቆስ መንበር ላይ የሚቀመጠው አባታችን በሚመረጥበት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ በር ለኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ክፍት እንዲሆንና መልክተኞቿ በምርጫው ውስጥ እንዲገኙ ፤

፬ኛ ፤ የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በእስክንድርያው ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ መንበር እንዲኖራትና ሲኖዶሱ በተሰበሰበ ቍጥር መልእክተኞቿ በሚገባቸው ደረጃ ተቀምጠው እንዲገኙ ፤

፭ኛ ፤ ኢትዮጵያ በውድ ሳይሆን በግድ በጦር ኃይል ከእስክንድርያ ጋራ እንዳትገናኝ ተከልክላ በተቋረጠችበት ጊዜ ፤ በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላም ዘመን እስክትደርስ መርጣ የሾመቻቸው ጳጳሳት ከግዝቱ እንዲፈቱላት ።

፮ኛ ፤ በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው የመንፈሳዊ ግንኙነት አሁን ካለው የበለጠ እንዲሆን የአንድነትና የልጅነትም መሠረት የጠነከረ ሆኖ እንዲኖር ፤ የገዳም ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ እንዲከፈት ፤ ስለዚሁም ተማሪ ቤት አቋቋምና አካሄድ ቅዱስ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ቅዱስ ቡራኬያቸውን እንዲሰጡን ። በዚህ ተማሪ ቤት ተመርቀው ለጵጵስና ወይም ለቍምስና የታጩት መምህሮች በምስር ገዳማት ውስጥ እየሄዱ ከወንድሞቻቸው ጋራ በመንፈስ ተባብረው እንዲመለሱ ፤ እንደዚሁም ከምስር የሚመጡት ወንድሞቻችን በኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ሲመጡ በመንፈሳቸው ሁሉ የተባበሩ ወንድሞች አግኝተው እንዲመለሱ » የሚል ነው ።

የጥያቄውም መልስ ከ፫ ወር የሚበልጥ ስለዘገየ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በኅዳር ፲፰ ፲፱፻፴፱ ዓ ም በደብዳቤ ያስታውስ ዘንድ ግድ ሆነበት ። ከብዙ ጉትጎታም በኋላ ስለ መልሱ በየካቲት ፳፱ ቀን ፲፱፻፴፱ የጻፉልን ደብዳቤ ለጊዜ ማርዘሚያ ያህል እንጂ ለሌላ የማይጠቅም መሆኑ ስለታወቀ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ቀጥተኛው መልሱ በቶሎ እንዲሰጣት እንደ ገና ሌላ የልመና ደብዳቤ በመጋቢት ፲፰ ፲፱፻፴፱ ዓ. ም. ተጻፈላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ ከግብጻውያን ጉባኤ በሰኔ ፱ ፲፱፻፴፯ ዓ ም ተጽፎ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተላከላት መልስ ከማሳዘኑ በቀር የስምምነቱን መንፈስ ለማጽናት የማይደግፍ ሆነ ።

የኢትዮጵያ ተወላጅ በገሩ ላይ የሊቀ ጳጳስነት ማዕርግ እንዲያገኝ ተብሎ በ፩ኛና በ፪ኛ ቍጥር የተጻፈውንና የተጠየቀውን ዋናውን ጉዳይ በፍጹም እንደማይቀበሉት እያረጋገጡ ፤ በኢትዮጵያ ሊሾም የሚገባው ሊቀ ጳጳስ ግብጻዊ ነው አሉ ።

በሌላው በታናናሹ ክፍል ግን በጉባኤጦ እንዲገኝ ለተባለውና ስለተማሪ ቤቱ አቋቋም ለተመለከተው ፤ ፈቃድ እንዳላቸው አስታወቁ ።

ከግብጽ የመጣው ይህ መልስ በሐምሌ ፮ ቀን በኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ ቀርቦ ከተነበበ በኋላ ፤ ግብጻውያን በኢትዮጵያ ፤ ግብጻዊ ሊቀ ጳጳስ እንጂ ኢትዮጵያዊ ሊሾም እንደማይችል ከወሰኑ፤ ይህ አስተያየት ዘራችንን የሚያሳንስ ፤ የነፃነት ክብራችንንም የሚቀንስ ነውና ፤ ኢትዮጵያ ራሷን ችላ መኖር ይገባታል ሲል ፤ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አስታወቀ ።

የንጉሠ ነገሥቱም መንግሥት የነገሩን አኳኋን ከተመለከተ በኋላ፤ ከጥንት ጀምሮ እንደቈየው ሥርዓታችን ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት የተባበሩ ስለሆኑ ፤ ይልቁንም የቤተ ክህነታችን ጠባቂዋና ደጋፊዋ ቤተ መንግሥታችን ስለ ሆነ ፤ መላክተኞቹን ወደ ግብጽ ለመላክና የመጨረሻ ቃላቸውን ለመቀበል አስቦበታል ።

በመልክተኞቹም እጅ የሚሄደው ቍርጠኛው ቃል በኢትዮጵያ የመላው አብያተ ክርስቲያናት መልክተኞች የሆናችሁት እናንተ ሊቃውንቱና መምህራኑ ከቤተ መንግሥት ጋራ ተባበራችሁ በምትወስኑት መሠረት እንዲሆን ስላስፈለገ እነሆ ለዚሁ ጉዳይ ተጠርታችኋል ።

ከያውራጃው በሕዝበ ክርስቲያን ድምፅ በሚገባ ተመርጣችሁ የመጣችሁ ሊቃውንትና በተለይም ለጉባኤው ተካፋይነት የተጠራችሁ ክቡራን የገዳማት መምህራን ሆይ፣

ሁሉን መርምሮ የሚያውቅ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር በእውነተኛው መንገድ እንዲመራን ፤ እውነተኛውንም ምክር እንዲገልጽልን እየለመንን ሥራችን እንጀምር ።

የአብ በረከት ፤ የወልድ ቸርነት ፤ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ፤ በሁላችን ላይ አድሮ ይኑር ።

ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፴፰ ዓ ም

አዲስ አበባ ።



## ሁለተኛ ክፍል ።

### በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና በኮፕት ቤተ ክርስቲያን መከከል ባለፉት ጊዜያቶች የተደረጉ ንግግሮችና ሁለቱም ወገኖች የተላላኩዋቸው አንዳንድ ደብዳቤዎች ።

፩

### ከታሪኩ በጭሩ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቋንቋዋ የሚሰብክላትና በመከራዋ ጊዜ የማይለያት ሊቀ ጳጳሳት ከተወላጆቿ ለማግኘት ስታስብበት የቆየ ነገር ነው ። በ፲፱፻፳፱ ዓ ም በኢትዮጵያ ሕዝብና ቤበተ ክርስቲያኒቱ ላይ ብርቱ መከራ ደርሶ ሳለ ሊቀ ጳጳሱ ወደ ሀገራቸው ወደ ግብጽ ገብተው ነበር ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስዋን በመከራ ጊዜ ከማይለይዋት ከተወላጆቿ ከመንፈሳውያን አባቶች መከከል ለማግኘት ከማያከራክረው ሰዓት ላይ ደረሰች ።

ሊቀ ጳጳሱ ወኪል ያደረጓቸው ጳጳሱ አቡነ አብርሃም በ፲፱፻፴ ዓ ም ኅዳር ፳፱ ቀን በሊቃውንት ሲኖዶስ (ጉባኤ) ተመርጠው ሊቀ ጳጳሳት ሆኑ ። ጳጳሳትንም ሾሙ ። እርሳቸውም ሲያርፉ ተከታያቸው አቡነ ዮሐንስ በሊቃውንት ሲኖዶስ (ጉባኤ) ተመርጠው የያውራጃው ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ቆሞሳትም ባሉበት ሊቀ ጵጵስናውን ተሾሙ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓይነት አስተዳደር በተወላጆቿ ተጠብቃ ሳለች ፤ ኢትዮጵያ ነፃነቷንና ንጉሠ ነገሥቷን ለማግኘት በቃች ።

በ፲፱፻፴፫ ዓ ም በመጋቢት ወር ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ የሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ግንኙነት ለማቃረብ መልክተኛ ይልኩ ዘንድ አስበው ጥያቄ ቢያቀርቡ ለጥያቄአቸው የቅንነት መልስ ተሰጣቸው ። እሳቸው ግን የስምምነቱ ጉዳይ ከመፈጸሙ አስቀድሞ የፊተኛው ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ መልክተኛ ሆነው ከሌሎች ተከታዮች ጋር እንዲመጡ አደረጉ ። ከንግግሩም በኋላ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያላት የስምምነት አሳብ ተገልጾላቸው የቀሩት መልክተኞች ሲመለሱ አቡነ ቄርሎስ ከዚሁ ቆዩ ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ጊዜ ከግብጻውያን በኩል በቀረበው አሳብ መሠረት ስምምነቱን ያለቅርታ በፍጥነት ለመፈጸም ምክንያት ይሆናል ተብሎ ታስቦ ስለ ነበረ የሊቀ ጳጳሳቱን መንበርና ግቢውን ይዘው በሥራው ላይ የነበሩት ኢትዮጵያዊው ሊቀ ጳጳሳት በ፲፱፻፴፬ በሰኔ ወር ግቢውን እንዲለቁ ተደረገ ። ቀጥሎም ስለ ትሕትና ሲባል የፊተኛው ሊቀ ጳጳስ እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ የጳጳሳቱም ከሥራ መቈየት የስምምነቱን ፍጻሜ እንዲጠብቅ ሆነ ።

ከዚህ በኋላ ነገሩን የሚያረዝመው ምክንያት እየበዛ ሄደ ። እንደ አጋጣሚም ፓትርያርኩ አቡነ ዮሐንስ በ፲፱፻፴፬ ዓ ም በሰኔ ወር ስላረፉ ሌላው ፓትርያርክ እስኪሾሙ ብዙ ወሮች አለፉ ። በሁለተኛው ዓመት በ፲፱፻፴፮ ዓ ም ሁለቱም ወገኖች አዲስ አበባ ላይ ስብሰባ አድርገው ንግግሩን እንደ ገና ጀመሩ ።

በዚህ ጊዜ የተደረጉት ንግግሮችና ከዚያም በኋላ የተላላኩዋቸው አንዳንድ ደብዳቤዎች ወደፊት ተጽፈው የሚገኙት ናቸው

---

፭

## በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ጉዳይ የተደረገ ንግግር ።

ስብሰባው በሰኔ ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፮ ዓ. ም. ከቀኑ በ፲ ሰዓት አዲስ አበባ በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ሣሎን ፤ በብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ሰብሳቢነት ተደረገ ።

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ከተከታዮቻቸው ጋራ ቀረቡ ።

ስለ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ዋናው መልክተኛ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስና ተከታዮቻቸው ቀረቡ ።

### የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ። በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው



ጉዳይ ካሁን በፊት ከብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ተልከው ለመጡት መልክተኞች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገውና መልክተኞቹም ሊያውቁት የሚፈልጉት ነገር በዝርዝር ተሰጥቷቸው ኼደው ነበር ። ይኸውም ጥያቄ በአቡነ ዮሐንስ ሞትና በአዲሱ ጳጳስ አለመሾም ምክንያት ዘግይቶ ስለ ነበረ ሳይፈጸም ቈየ ። አሁን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች የሆናችሁ እናንተ ሰፊተኛው ጥያቄያችን ምን መልስ አመጣችሁልን ? ብለው ጠየቁ።

### የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች መልስ ።

ካሁን በፊት የመጡት ሰዎች አቡነ ቄርሎስን እንዲከተሉና የግዝቱን ጉዳይ እንዲመረምሩ ነው እንጂ ከዚህ የተሰጣቸውን ጉዳይ ለመቀበል አልተላኩም ነበር ። ይሁን እንጂ እዚህ በነበሩበት ጊዜ የተሰጣቸውንና ያገኙትንም ለብፁዕ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት አስታውቀዋል ።

ያነኑ ጉዳይ የሚነጋገሩ ሰዎች እንዲላኩ ሲል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትን ጠይቆ ይምጡ የሚል መልስ ካገኘን በኋላ ነው የመጣነው ። ይሁን እንጂ የፊተኞቹ መልክተኞች የቤተ ክህነትን ጉዳይ የማያውቁ ስለ ነበሩ አሁን በጉዳዩ ሊነጋገሩ የሚችሉትን አቡነ ጢሞቴዎስን ፓትርያርኩ ልከዋቸዋል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንንም ጥያቄ ያጠናነው ስለ ሆነ አሁን ንግግሩን ለመቀጠል ይቻላል ብለው ንግግራቸውን በመቀጠል እንዲህ አሉ ።

በቀረበው ራፖር እንደ ተመለከትነው ፩ኛ ጥያቄ ከኢትዮጵያውያን ፩ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾም ነው ። ለዚሁም የተሰጠው ምክንያት ያገሩን ቋንቋና ልማዱንም ሁሉ የሚያውቀው ስለ ሆነ ኢትዮጵያውያኖችን በልዩ ልዩ ሃይማኖት ከኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው እንዳይለወጡ ለማድረግ የሚቀናው በመሆኑ ነው ተብሏል ።

### የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች የተናገሩት ።

« ከዚህም ከነተነገረው ምክንያት በቀር ሌላም አለ ። ፩ኛ ቋንቋውንና የሕዝቡን ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ በማወቅ የቤተ ክርስቲያናችንን አስተዳደር ለማሻሻል የሚቻለው ያገር ተወላጅ ሊቀ ጳጳስ

www.ethiopianorthodox.org

ሲገኝ ነው ። ፪ኛ ባለፉት የመከራ ዘመኖች እንደ ተደረገው ሁሉ ለምሳሌ እንደ አቡነ ጴጥሮስና እንደ አቡነ ሚካኤል ፤ እንደ ደብረ ሊባኖሶችና እንደ ዜና ማርቆሶች ፤ እንደ ማኅበረ ሥላሴዎችም ለሕዝቡ በመንፈስ መጽናኛ የሚሆኑና ለሃይማኖታቸውም ለኢትዮጵያ መሥዋዕት የሚሆኑላት በመከራ ጊዜ የማይለዩ የገር ተወላጆች ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንዲኖሯት ያስፈልጋል ። ፫ኛ እንዳለፈው ጊዜ አደጋ ሆኖ መንገድ ሲቋርጥ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠላት ካገር የማያስወጣው የራስዋ ሊቀ ጳጳሳት ሊኖ ራት ይገባል ። ፬ኛ በብዙ የሃይማኖት ወረራ ስትፈተን ከሺ፮፻ ዘመን ይበልጥ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላትን አን ድነት ሳታቋርጥ በታማኝነት የኖረች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፩ ሊቀ ጳጳስ ከቤተ ሰቦቿ ለማግኘትና ይኸውም ሊቀ ጳጳስ ጳጳ ሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ሥልጣን የተሰጠው እንዲሆን ትፈልጋለች ። ይኸውም ሲሆን የኢትዮጵያና የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት አንድነታቸው የፀና ሆኖ ስለሚኖር የምን ጠይቀው ሊቀ ጳጳስ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ሥልጣን እን ዲሾም ነው › አሉ ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች የሰጡት መልስ ።

፩) ከኢትዮጵያውያን ሊቀ ጳጳስ የመሾሙ ጉዳይ የጉባኤ ኒቅ ያንን ውሳኔ የሚነካ በመሆኑ የሁለታችንንም ቤተ ክርስቲያኖች መሠረት የሚያፈርስ ስለ ሆነ እጅግ አስቸጋሪ ጉዳይ ነው ።

፪) ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስነት የሚሾመው ግብጻዊ የአማርኛን ቋንቋ አጥርቶ የሚያውቅ እንዲሆን በመታሰቡ ፤ በውስጡ ሆነው ከሚሾሙት ኢትዮጵያውያን ጳጳሶች ጋራ በኅብረት የሚሠራ ሲሆን ልጆቹን ከሃይማኖት መለወጥ ለማዳንና የቤተ ክርስቲያና ችንም ደንብ ለማሻሻል የሚበቃ ችሎታ ይኖረዋል ።

፫/ ሺ፮፻ ዘመን ያህል በኢትዮጵያ የነበሩት ጳጳሶች በገሩ ላይ ከደረሰው ፈተና ተካፋይ በመሆን በጦርነትም የሞት ተካፋይ መሆ ናቸው ይዘነጋ አይመስለንም ። በጠላትም አስገዳጅነት ግብጻዊው ጳጳስ



ካገር እንዲወጣ ቢሆን በውስጡ ካሉት የኢትዮጵያ ጳጳሳቶች አን ዱን በወኪልነት እንዲሠራ ሥልጣን ሊሰጠው ይቻላል ብለው መለሱ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

ባለፈው ጊዜያት ኢትዮጵያን የወረራት ፋሺስት አቡነ ቄርሎ ስን ካገር ሲያስወጣና በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ የተሾሙትን የኢትዮጵያን ጳጳሳት ከአቡነ አብርሃም በቀር ሲገድል የአቡነ ቄርሎስ ወኪል የነበሩት አቡነ አብርሃም ዓይናቸው ተሰውሮ በሕመማቸው ምክንያት የዕድሜያቸው ፍጻሜ መቅረብ ሲሰማቸው ከእስክንድርያው ጳጳስ ጋራ ለመገናኘት በፍጹም የማይቻል በመሆኑ ሃይማኖታቸውን ለማዳን የሊቃውንት ስብሰባ አድርገው ጳጳሳትን ከው ስጣቸው ቢመርጡ የእስክንድርያ መንፈሳዊ ጉባኤ በውግዘት ከመለየት በቀር ለተደረገባቸው ችግር እርዳታ ሊያደርግላቸው አልቻለም ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች መልስ ።

በፊት የተሾሙት ጳጳሳቶች እንደተለመደው ሥራቸውን ቀጥለው ቢሆን ባልተወገዙም ነበር ። ውግዘት የሆነው ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን መለየትን በማወጃቸው ነው አሉ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች መልስና ጥያቄ ።

‹የአቡነ ቄርሎስ ወኪል የነበሩት አቡነ አብርሃም ከእስክንድር ያው ጳጳስ ጋራ የሚገናኙበትን መንገድ ከማጣታቸው የተነሣ የኢት ዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖት አባት እጦት ምክንያት ከባዕድ ሃይ ማኖት ወረራ ለማዳን ጉባኤ አድርገው ጳጳሳትን ሾሙ ። ይህንስ ባያደ ርጉ ምን መንገድ ይገኝለት ኖራል? ። በነሱስ ቦታ እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ኖሯል?።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች መልስ ።

በአውሮፕላን፥ ወይም በነፋስ ስልክ መገናኘት ይቻል ነበር አሉ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች መልስ ።

በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ባትኖሩ ነው እንጂ ፤ የነበሩት አውሮፕላ ኖችና የነፋስ ስልኮች የኢጣልያኖች ብቻ እንደነበሩ ትረዱት ነበር አሏቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሳይገኝ ቀርቶ በጉባዔ ኒቅያ ተወስኗል በተባለው ጉዳይ ንግግራቸውን ሲቀጥሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች በጉባኤ ኒቅያ ውሳኔ ላይ ኢትዮጵያውያኖች ሊቀ ጳጳስ አይሹሙ ይላል እንጂ ራሳቸው አይሹሙ አይልም አሉ ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

በዓረብኛ በተጻፈው ላይ አይሹሙ ደግሞ አይሾሙ ነው የሚለው አሉ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

እናንተ በዓረብኛ የተጻፈውን ቃል መሠረት ስታደርጉ እኛም በግዕዝ የተጻፈውን መሠረት በማድረግ የተለያየ ቃል ቢኖርበት ጥንታዊ ጽሑፍ በግሪክ ስለ ሆነ ከግሪክ ሊቅ መርጠን እናስተርጉመው ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

፲፮፻ ዘመን በኢትዮጵያውያን፡ሊቀ ጳጳስ ሳይሾም መኖሩ ጉባኤ ኒቅያ የማይፈቅድ መሆኑን ያስረዳል ሲሉ መለሱ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

እስከ ዛሬ ሳንጠይቅም ብንቄይ ዛሬ በማወቅና ለጊዜውም አስፈላጊ በመሆኑ ጳጳስ እንዲሾምልን ብንጠይቅ የጊዜው መቆየት የጉባኤ ኒቅያን ጽሕፈት የሚለውጠው አይደለም ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

የሁለት አገሮች ቤተ ክርስቲያኖች ባንድ ጳጳስ መተዳደር ያገሮቹን ክፍታና ዝቅታ የሚያሳይ አይደለም ። ይህም ሊታወቅ ፈረንሳዊ፥ እስፓኝ፥ፖርቱጋልና ሌሎችም አገሮች በሮማ ጳጳስ ይተዳደራሉ ሲሉ ምሳሌ አደረጉ ።



የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

እኛም ከነዚህ ከተቈጠሩት አገሮች የተለየ መብት ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን አልጠየቅንም ። ፈረንሳዊ፥ እስፓኝና ፖርቱጋል የሚያስፈልጓቸውን ጳጳሶች ከገራቸው ሰዎች በሮማ ጳጳስ ያሾማሉ እንጂ የሮማው ጳጳስ የኢጣልያን ተወላጅ የሆነውን ሰው እየሾመ አይልክባቸውም ብለው መለሱ ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

የሮማ ጳጳስ በያገሩ እንደራሴዎች አሏቸው እኮ አሉ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ሆኖ አንድነታችንን የሚያጸና መልክተኛ ቢኖራቸው ችግር ነገር ያለበት መስሎ አይታየንም ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

ሊቀ ጳጳስ ይሾም መባሉ ለክብር ብቻ ነው እንጂ እርሱ የሚያደርገውን ጳጳሳቶች ሊያደርጉት ይችላሉ ። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ጳጳሶች ሲኖሩ ለቤተ ክርስቲያኑ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ ለማድረግ ይችላሉ አሉ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

፲፮፻ ዘመን ያህል በመከራና በዓለምም ጊዜያቶች በማርቆስ ሃይማኖት ጸንተው ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላቸውን ግንኙነት ጠብቀው ለኖሩት ለኢትዮጵያውያን ልጆቻቸው ሊቀ ጳጳሱ ለግብጻውያን በሚያደርጉት እኩልነት ለምን ይነፍጉናል ብለው ጠየቁ ።

የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

ሊቀ ጳጳሱ ኢትዮጵያውያንን በመውደዳቸው በግብጽ ውስጥ ጳጳሳቶች እያሉ ሲሾሙ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ብለው ይሾሟቸው ሲሉ መለሱ ።

www.ethiopianorthodox.org

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

እንግዲህ የጠየቅነው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ በስምምነትና በወዳጅነት የሚሾምልን ነውን ? ወይስ አይቻልም ነው የምትሉን ? ብለው ጠየቁ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

ይህን ጉዳይ ሳንሲኖድ የተባለው የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ታላቁ ጉባኤ መክሮበት የሚቈረጥ ነው እንጂ ፣ ይሆናል ፤ ወይም አይሆንም ማለቱ የኛ መብት አይደለም ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

ጉዳዩ በሳንሲኖድ ጉባኤ የሚቈረጥ መሆኑ እርግጥ ነው ። ይኸውም ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ብርቱ ጉዳይ ስለ ሆነ የብፁዕ አቡ ጢሞቴዎስና የናንተም የመልክተኞቹ መልካም አስተያየትና እርዳታ እንዲሰጠው ተስፋ እናደርጋለን አሉ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

የጉዳዩን ታላቅነት እናውቃለን ። ይህም ነገር በሚቈረጥበት ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች እንዲከራከሩበት በጉባኤው ላይ እንዲገኙ ተስፋ አለን ቢሉ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች የኢትዮጵያ መልክተኛ ሂዶ እንዲነጋገር አስፈላጊ መሆኑ የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ በጉባኤ ኒቅያ ትርጉም የማንስማማ ቢሆን በጉባኤ ኒቅያ ከነበሩት ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ አማካይ ተርጓሚዎች ለመምረጥ ይቻል የለምን ሲሉ ጠየቁ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

የዚህ ዓይነት ትርጉምና የሐሳብ መለያየት ቢያጋጥም ሁለታችንም ወገኖች በግሪክ ቋንቋ ሊቃች የሆኑ አርቶዶክሳውያን ሰዎች ለመምረጥ ይቻላል ሲሉ አስታወቁ ።

ከዚህ በኋላ የሚቀረውን ጉዳይ በሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ ም በ፲ ሰዓት ተኩል በዚሁ በታ ሁለቱም ወገኖች ተሰብስበው ንግግራቸውን እንዲቀጥሉ ቀጠሮ ተደረገ ።

---



## በኢትዮጵያና በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን
## መካከል ስላለው ጉዳይ ፣
## የተደረገ ንግግር ።

ስብሰባው በሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ ም ከቀኑ በ፲ ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ በቤተ መጻሕፍት ወመዘክር ማሉን በብፁዕ ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ ሰብሳቢነት ተደረገ ።

የተሰበሰቡት ወገኖች በፊተኛው ስብሰባ የነበሩት ናቸው ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች የተናገሩት ።

ለቤተ ክርስቲያናችን ያስፈልጋሉ የምንላቸውን ታላላቅ ጉዳዮች ባለፈው ስብሰባ ነግረናችኋል ፤ አሁን የሚቀሩት በመሠረቱ ጉዳይ ስንስማማ ተከታይ የሚሆኑ ዝርዝሮች ናቸው ። ይኸውም ታላቅ ጉዳይ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾምልን የጠየቅነው ነው አሉ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

የሊቀ ጳጳሱ ሹመት ጉዳይ የሚወሰነው በታላቁ የእስክንድርያ ጉባኤ መሆኑን አስረድተን ፣ በክርክሩም ላይ የኢትዮጵያ መልክተኞች እንዲኖሩ ተስማምተንበታልና ወዳለቀው ጉዳይ ሳንመለስ የእስክንድርያንና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያኖች ከለፈው ጊዜ ይበልጥ ለማቅረብ የሚያስፈልጉትን ነገሮች አስረዱን ሲሉ ጠየቁ ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

የእስክንድርያው ታላቅ ጉባኤ በሚሰበሰብበት ጊዜ የኛም መልክተኛ ፤ ከጉባኤው ላይ እንዲገኝ የተስማማነው ፤ በኢትዮጵያ የክርስቲያን ሃይማኖት ከመሰበኩ አስቀድሞ በ፬፻፶፩ ዓ ም በጉባኤ ኒቅያ ተጻፈ በተባለው ምክንያት የጳጳሱን መሾም ሳይፈቅድ የቀረ እንደ ሆነ በጉባኤ ኒቅያ የተሰበሰቡ ሊቃነ ጳጳሳት ፤

፩ / የሮማ ቤተ ክርስቲያን ( ኢጣሊያ )

፪ / የቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ( ግሪክ )

www.ethiopianorthodox.org

፫ / የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ( ሶርያ )
፬ / የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ( ግብጽ )

በመሆናቸው ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቤተ ክርስቲያኖች የጉባኤ ኒቅያ ጽሑፍ የሚገኝ ስለ ሆነ ፤ ነገሩን በነርሱ ለማሳየት የምንችል እንደሆነ ስንስማማበት ነው አሉ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

በጉባኤ ኒቅያ የተሰበሰቡት ፤ እንዳላችሁትም ያሬቱ ቤተ ክርስቲያኖች ጳጳሳቶችና ምእመናኖች ናቸው ፤ ይሁን እንጂ አሁን ተቆያይተን እንደ ባላጋራ የምንተያይ ስለ ሆነ፤ የእስክንድርያው ታላቁ ጉባኤ የሚወስነው ሳይታወቅ ለአማካይ ዳኝነት የሚመረጠውን ቤተ ክርስቲያን መወሰን አስፈላጊ አልነበረም ፤ ይሁን እንጂ በእስክንድርያው ታላቅ ጉባኤ የሚወሰነው የማይስማማችሁ በሆነ ጊዜ ወደ ወደዳችሁት አርቶዶክሳዊ ቤተ ክርስቲያን ነገሩን እናስማለን ብትሉ እኛ መልክተኞቹ አስቀድመን የምንቃወም አይደለንም ብለው መለሱ ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

ምንም በልምዱ ለእስክንድርያ ፓትረያርክ ሆና የሚሾመው ግብጻዊ ቢሆን በሃይማኖትና በወንድማማችነት እኩልነት ያለን ስለ ሆነ፤ የእስክንድርያ ፓትረያርክ ለመሆን ኢትዮጵያውያንን የሚከለክል ነገር አለመኖሩ የታወቀ ሁና ፓትረያርኩን ለመምረጥ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ድምፅ እንዲኖራት ያስፈልጋል ። የሁለቱንም ቤተ ክርስቲያኖች አንድነትና ፍቅር ለማጽናት በትምህርትና በአስተዳደር የተመሳሰሉ እንዲሆኑ ያሻል ፤ ስለዚህ ትምርት እንዲሰፋ ቢደረግ ፤ ከዚህም ይልቅ የሃይማኖት ወደረኞቻችን የሆኑ በብዙ ትጋትና ድካም ሃይማኖት የሌ



ላቸውን ወገኖቻችንን ስለሚሸሙን ከለፉት ጊዜያቶች ይበልጥ አንድነታችንን አጽንተን የስብከትና የትምህርት ሥራችንን ማስፋፋት ይገባናል ሲሉ አስረዱ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የጠየቁናቸውን ነገሮች ሁሉ መርምረን የተረዳን ስለ ሆነ ፤ በቀና መንፈስ ለአቡነ መቃርዮስ ማልሳዊ ነገሩን እናስረዳለን ። በአቡነ ጢሞቴዎስ ፕሬዚዳንትነት የተላክነው መልክተኞች ከዋናዎቹ ጉዳዮቻችን አንደኛው ትምህርት የሚሰፋበትን ነገር ማጥናት ስለ ሆነ ፤ ከዚህ ለትምህርት ቤት የሚሆኑ ሕፃናቶችና ሌላም የምታደርጉልንን እርዳታ ከወቅነው ፤ ያሏ ተማሪዎቹ መላክ እርግጥ ነው ። እነዚህንም ቤቶች ከመሄዳችን በፊት ብናይ ደስ ይለናል ብለው አስታወቁ ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

የትምህርት ቤት ለማቆም የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የምትፈቅድ ስትሆን በበኩላችን የምናደርገው እርዳታና የምንሰጠው ቤት ከመሄዳችሁ በፊት ስናንተ በምንሰጠው ማስታወሻ ላይ ይመለከታል ሲሉ ከጨረሱ በኋላ ንግግራቸውን ቀጥለው ፤ በጉባኤ ኒቅያ የተሰበሰቡት ፫፻፲፰ ሊቃውንቶችና ጳጳሳቶች ፤ ኢትዮጵያውያን የክርስቲያንን ሃይማኖትን የተቀበሉ እንደ ሆነ ጳጳስ እንዳይሾሙና ለጳጳስነትም እንዳይሾሙ ሲሉ ከክርስቲያንነታችን በፊት ደነገጉ ሲባል ይህን ያደረጉበትን ምክንያት ሊያስረዱን ይችላሉ ወይ ? ብለው ጠየቁ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

ከየነገዱ የተሰበሰቡት ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንቶች ረዥም ጸሎት ካደረጉ በኋላ በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው የጻፉት ከመሆኑ በቀር ስለኢትዮጵያ የጻፉበትን ምክንያት ለይተን እናውቅም ሲሉ መለሱ ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች

እንግዲህ የኛን ጥያቄና ሐሳብ በረዥሙ የተረዳችሁት መልክተኞች በብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ማልሳዊ ዘንድና በታላቁ ጉባኤ ፊት የጉዳያችን ደጋፊና ጠበቆች እንድትሆኑን ስንለምናችሁ ጉባ

www.ethiopianorthodox.org

ጳስ ማጣት ምክንያት ያለብን ችግር ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ሣልሳዊ ተረድተውት በዚህ ጉዳይ እን ዲረዱን ተስፋ አለን ። ባ፲፪ቱ አውራጃ አገሮች ፲፭ ሺሕ የሚያህሉ አብያተ ክርስቲያናትና ከስምንት ሚሊዮን የሚበልጡ ክርስቲያኖች ስላሉ ከእስክንድርያ እንዲሾምልን የመንፈልገው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት የነዚህ አብያተ ክርስቲያናትና የምእመናን ሁሉ አለቃ ነው። የሚመረጠውም በነዚሁ ፲፭ ሺሕ ያህል በሆኑት አብያተ ክርስቲያ ኖች ድምፅ እንዲሆን የታሰበ ነው ብለው አስረዱ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች

የጳጳሶቹ አመራረጥ በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሕግ ዓይ ነት እንዲሆን ሲቍረጥ የደንቡን ግልባጭ ለመስጠት ደስ ይለናል ፤ ይኸውም ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወኪል በእስክንድርያው ታላቅ ጉባኤ ውሳኔ እንዲኖር ማድረግ ይቻላል አሉ ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ። ብፁዕ አቡነ ጢሞቲዎስን ፕሬዚዳንት አድርገው ለጕዳ ያችን ማጥናት የላኩአችሁን ብፁዕ አቡነ መቃርስ ሣልሳዊንና እና ንተንም መልክተኞቹን አመስግናለሁ ። እኛም የሁለታችንን ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ፈላጊዎች ነን ብለው ንግግራቸውን ጨረሱ ።

## የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ።

እዚህ ከመጣን ያየነውንና ያወቅነውንም ስንነግራቸው ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ሣልሳዊ በመልካም መንፈስ እንዲቀበሉት እናምናለን ። የኢትዮጵያ ምእመናንም በእምነትና በጸሎት ፤ በሃይማኖትም ሕግ አጠ ብቆ እጅግ ደስ የሚያሰኙ ስለ ሆነ በትምህርት በኩል የጳጳሱ እር ዳታ ማድረግ አርግጠኛ ነው ። የመጣንበትንም ጕዳይ ለማቃናት የረ ዳችሁንን ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስንና እዚህም የተሰበሰባች ሁትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተነጋጋሪዎች ከልብ እናመሰግናለን ብለው ንግግራቸውን ጨረሱ ።



ከዚህ በኋላ ወደ ግብጽ ከመመለሳችን በፊት በቅርብ የሚገኙ ትን ገዳማቶች እንድንጐበኝ ይፈቀድልን ሲሉ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች ስለ ጠየቁ የደብረ ሊባኖስን ገዳም ከብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ጋራ ሄደው ሊጐበኙ ተስማምተውበት ተለ ያይተዋል ።

ዲያቆን ስሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271603
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በ፲፩ ሰኔ ፲፱፻፶፩ ዓ. ም. ጽር ሐብዐቀ አቡነ መቃርዮስ የላከውና ፮ ጥያቄዎች የተመለከቱበት ደብዳቤ ።

መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ዘመንግሥተ ፡ ኢ ትዮጵያ ፡

አ.አ. ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም

የኦርቶዶክሳዊት፡ተዋሕዶ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡
ጠቅላይ፡ጽሕፈት፡ቤት ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ፡ ለብፁዕ አባታቸው ለሊቀ ጳጳሳት አቡነ መቃርዮስ የትሕትና ሰላምታቸውን እያቀረቡ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ተቀምጠው ይባርኳቸው ዘንድ ስለ ተመረጡ ደስታቸውን ይገልጻሉ ።

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ሐሳብ ሲያቀርቡ ብፁዕ አባታቸው አቡነ መቃርዮስ በነገሩ በጣም እንዲያስቡበትና መልካም ፍጻሜ እንዲያስገኙላት ተማምነው ነው ።

ብፁዕ አባታችን ሆይ ።

ኢትዮጵያ በፋሺስት መንግሥት በተወረረችበት ሰዓት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተለይታ እንድትኖር የጠላት መሠረት ሐሳብ መሆኑ ታውቋል ።

በፊተኞችም ዘመናት ውስጥ በኢትዮጵያ ላይ የጦር አደጋ በደረሰ ቍጥር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ መገናኛዋ እየተቋረጠባት የመከራው ዘመን እስኪያልፍ ድረስ ራሷን ችላ መኖሯ የታወቀ ነው ። የመከራውንም ዘመን በሃይማኖቷ ጸንታ ወደ ሰላሙ ዘመን በደረሰች ቍጥር እማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጠውን አባቷን ከመፈለግ አቋርጣ አታውቅም አሁንም ወደፊት ያላት ምኞት ይኸው መሆኑን ስትገልጽ ደስ ይላታል ።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ባለማግኘቷ ምክንያት በኢትዮጵያ ላይ አደጋ በመጣ ቍጥር ለክርስቲያን የሚ



ገባውን ሥርዓት ሁሉ ለኢትዮጵያ ምእመናን ለማድረግ አልቻለም። በዚህም ምክንያት ወደ ሌላ ሃይማኖት የሄዱና የሌላውን ሃይማኖት ባህል የለመዱ ብዙ ኢትዮጵያውያን ናቸው ።

ስለዚህ ወደፊት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ማርቆስን አባትነት ሳትለቅ ፤ ሃይማኖቷ የሚጸናበትንና ምእመናኖቿም የሚጠቀሙበትን መንገድ ለመመሥረትና ለመከተል ግዴታ እንዳለባት ስለ ተገነዘበች የሚከተሉትን መብቶች እማርቆስ መንበር ላይ የተቀመጡት ቅዱስ አቡነ መቃርዮስ ባርከው እንዲሰጧት ትለምናለች ።

፩ኛ ፡ ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ በቤተ ክህነት ክፍል አድገው ፡ በሃይማኖቷ ጸንተው ከሚኖሩት ከመንፈሳውያን አባቶች ለሊቀ ጳጳስነት የሚገባው ሰው ተመርጦ በእስክንድርያው አባታችን ተባርኮና ተቀብቶ እንዲሾምላት ፤

፪ኛ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሲኖዶስ በሚመረጥበት መሠረት የኢትዮጵያም ሲኖዶስ ፤ ለጵጵስናና ለኤጲስ ቆጶስነት የሚገቡትን ፤ መንፈሳውያን አባቶች እንዲመርጥና ከእስክንድርያ አባታችን ተቀብቶ የመጣው ሊቀ ጳጳስ ባርኮ እንዲሾማቸው ፤

፫ኛ ፤ በማርቆስ መንበር ላይ የሚቀመጠው አባታችን በሚመረጥበት ጊዜ የቅዱስ ሲኖዶስ በር ለኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ክፍት እንዲሆንና መልክተኞቿ በምርጫው ውስጥ እንዲገኙ ፤

፬ኛ ፤ የኢትዮጵያም ቤተ ክርስቲያን ዘወትር በእስክንድርያው ቅዱስ ሲኖዶስ ውስጥ መንበር ፤ እንዲኖራትና ሲኖዶሱ በተሰበሰበ ቍጥር መልክተኞቿ በሚገባቸው ደረጃ ተቀምጠው ፤ እንዲገኙ ፤

፭ኛ ፤ ኢትዮጵያ በውድ ሳይሆን በግድ ፤ በጦር ኃይል ከእስክንድርያ ጋራ እንዳትገናኝ ተከልክላ በተቋረጠችበት ጊዜ በሃይማኖቷ ጸንታ ፤ ወደ ሰላም ዘመን እስክትደርስ መርጣ የሾመቻቸውን ጳጳሳት ከግዝቱ እንዲፈቱላት ፤

፮ኛ ፤ በኢትዮጵያና በእስክንድርያ መካከል ያለው የመንፈሳዊ ግንኙነት አሁን ካለው የበለጠ እንዲሆን የእናትነትና የልጅነ

www.ethiopianorthodox.org

ትም መሠረት የጠነከረ ሆኖ እንዲኖር ፤ የገዳም ትም ህርት ቤት በዲስ አበባ እንዲከፈት ፤ ስለዚሁም ተማሪ ቤት አቋቋምና አከሄድ ቅዱስ አባታችን አቡነ መቃር እንዲሰጡን ። ከዚህ ተማሪ ዮስ ፤ ቅዱስ ቡራኬያቸውን ቤት ተመርቀው ለጵጵስና ፤ ወይም ለቁምስና የታጩት መምህሮች በምስር ገዳማት ውስጥ እየሄዱ ከወንድሞቻቸው ጋራ በመንፈስ ተባብረው እንዲመለሱ ፤ እንደዚሁም ከምስር የሚመጡት ፤ ወንድሞቻችን በኢትዮጵያ ገዳም ውስጥ ሲመጡ በመንፈሳቸው ሁሉ የተባበሩ ወንድሞች አግኝተው እንዲመለሱ ።

ከዚህ በላይ በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱት ጉዳዮች ለእስክንድርያና ለኢትዮጵያ አንድነት ዘለዓለማዊ መሠረት መስለው የሚታዩን ናቸው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደሌሎቹ አርቶዶክሳውያን ብቸኝነትን አትፈልግም ። ከእስክንድርያ ጋራ በአንድነቷ ጸንታ ለመኖር ስለፈለገች ነው መለያየት የሚያመጡትን ምክንያቶች ሁሉ ለማስወገድ የወደደችው ።

እነዚህን በስድስቱ አንቀጾች የተመለከቱትን ጉዳዮች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ሆኖባት የጠየቀችበት ምክንያት፤ ከብፁዕ አባታችን ተልከው ከመጡት ሰዎች ጋራ በተደረገው ጉባኤ የንግግር ማስታወሻ ውስጥ ይገኛል ።

ይልቁንም በአንደኛውና በሁለተኛው አንቀጽ ውስጥ የተመለከቱት ዋናዎቹ ጥያቄዎች ለቀድሞው ጊዜ አስፈላጊ አይደሉም ተብለው ተደንግገው እንኳን ቢሆን የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ መንፈስ በፍጹም አልተቀበለውም ።

ስለዚህ ብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ የሐሳባችን ተካፋይ ሆነው ፤ የኢትዮጵያንና የእስክንድርያን መሠረት ለማናወፅ የተነሡትን ነፋሳት በተሰጣቸው በታላቁ ረድኤት ለማስወገድ እንዲደክሙበትና እንዲችሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አጥብቃ ታሳስባለች።

ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ
ዜነበረ በመንበረ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ።



. ፮ .

የእስክንድርያ ፓትሪያርክ በየካቲት ፳፪ ፲፱፻፴፯ ዓ. ም.
(1.3.45.) የጻፉት ደብዳቤ ።

ካይሮ ፳፪ አምሺር ፲፮፻፷፩
(የካቲት ፳፪ ቀን ፲፱፻፴፯)

በጣም ለተወደዱ ልጃችን ፤ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ።

ቡራኬያችንን እየሰጠንዎ እንደዚሁም ከፍ ላለው ሰውነትዎና ለተባረኩት ልጆቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጸሎታችንን ለእግዚአብሔር እናቀርባለን ።

በእኔ ሰብሳቢነት የተሰበሰበው የቅዱስ ሲኖድ ጉባኤ ሊነካ የማይቻለውን የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ልማድ መሠረት አድርጎና እንደዚሁም በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ያሉትን መገናኛዎች ለማጽናት ዋና አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መሠረት አድርጎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ሁሉ በታላቅ ጥንቃቄ መርምሯል ።

ምርመራ ባደረግን ጊዜም በተለይ የተመለከትናቸው አንድ አንድ ጉዳዮች ስላሉ ስለነዚሁ ነገሮች ለግርማዊነትዎ መጻፍ አስፈላጊ ስለ መሰለን ስለ መጨረሻው ንግግር የኢትዮጵያን መልክተኞች ለመጥራት እንድንችል ግርማዊነትዎ መልሱን በፍጥነት እንዲልኩልን እንለምናለን ።

በተለይ የተመለከትናቸውም ነገሮች እነዚህ ናቸው ።

፩/ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልክተኞች በሰኔ ፳፩/፴፮ (27.6.44) ከቀረቡልን ጥያቄዎች መካከል አንዱ ጥያቄ አምስተኛው ነው ። ቃሉም የሚከተለው ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያላትን ግንኙነት የጦር ኃይል ቈርጦባት በነበረ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተገድዳ ሃይማኖቷን ጠብቃ ለማኖር ስትል የመረጠቻቸው ጳጳሳት ውግዘት እንዲፈታ ፤

፪/ እነዚህ ያለሕግ ከተቋቋመ ባለሥልጣን የመንፈሳዊን ሥልጣን በተቀበሉ ጊዜ የተወገዙት ጳጳሳት (እስኮፍ) ያላንዳች ውልና ያላ

www.ethiopianorthodox.org

ንዱች ነገር ፡ መብት ከሌላቸው ሰዎች የመንፈሳዊን ሥልጣን በመቀበ ላቸው ማናቸውም ዐይነት የመንፈሳዊ ቅጣት ሳይደረግባቸውና ክነሱም ጳጳሶች ወገን መጻጽታቸውን ፤ ወይም ማዘናቸውን ሳይገ ልጹ ውግዘቱ እንዲፈታ ግርማዊነትዎ አስቀድሞም የቅዱስ ሲኖድን ጉባኤ ጠይቶ ነበር ። የቅዱስ ሲኖድ ጉባኤም በሰኔ ፲፱ ፲፱፻፴፬ (26. 6. 42.) ባወጣው ትእዛዝ እያንዳንዳቸው አስቀድሞ ያላቸውን ሥልጣን እን ዲይዙ ተደርጎ እነዚህን ጳጳስ የተባሉትን ያወገዘው ቃል እንዲ ፈታ አውጆ ነበር ።

፫/ ከነዚሁ ከተባሉት ጳጳሶች (አስኮፍ) አብዛኛዎቹ አኳኋ ናቸውን ምንም ያልለወጡ መሆናቸውንና ያንኑ ልብሳቸውን የጳ ጳስ ልብስ ለብሰው በዋናው ከተማ መቀመጣቸውን ከአቡነ ኤል ሙጥራን ጋራም ግንኙነት ያለማድረጋቸውን ሰምተናል ። ለኛ መታዘዛቸ ውን በሥራቸውም የመጸጸታቸውንና የማዘናቸውን ተግባር ለመፈጸም ይህም ቢቀር በነፍሳቸው ጥፋት ጊዜ የግዝቱን ቃል በመፍታት ስላደረገላቸው በጎ አድራጎት የቅዱስ ሲኖድን ጉባኤ ለማመስገን ከኛም ጋራ ግንኙነት አላደረጉም ። . . . .

፬ ፡ ለነዚህ ሰዎች ስለተጠየቀው ነገር በጣም የተጣራ ነገር አልተመለከተም ። አሁን የሚጠየቀው (የምትጠይቁት) እነዚህ በሕግ ካልተቋቋመ በስሥልጣን የመንፈሳዊ ሥራ ሥልጣን የተቀበሉና በኋላም ከዚሁ ሥልጣን የተከለከሉ ሰዎች እንደ አስኮፍ እን ዲቄጠሩና ደግሞ እንደ ገና አስቀድሞ ተሾመው ለነበሩበት አገር እንዲሾሙ ነውን ።

፭ ፡ እንደዚህ እንደ ሆነ ስለዚህ ነገር ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የሚያስፈልጉትን ማለት በሀገሩና በልዩ ልዩ አውራጃዎች ያሉትን ገዳሞችና ቤተ ክርስቲያኖች በመመልከት የቤተ ክርስቲያን ጥቅሞች በተሻለ ደንብ የተጠበቁ እንዲሆኑ ሲደረግ የታሰበው አከፋፈልና የሚቋቋመውን ጠቃሚ ሥራ ማወቅ ዋና ነገር ነው ።

፮ ፣ ደግሞም እነዚህን ጥያቄዎች ያቀረቡልንን የቤተ ክህነት ሰዎች ለማወቅ በጣም እናስባለን ። እንደዚሁም እነዚሁ ሰዎች በሀገሩ ውስጥ የተቋቋሙትን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ክፍ



ሎች ይልቁንም ገዳሞቹን ፤ የገዳሞቹን አለቃዎችና መነኰሴዎች እን ደምን እንደሚያስተዳድሩ ለማወቅ እናስባለን ።

፯ ፡ ደግሞም ለቤተ ክህነት ሥራ ከመመረጣቸው አስቀድሞ የእነዚህን ጳጳስ የተባሉትን የየአንዳንዳቸውን ልዩ አኳኋን የሃይማ ኖት ትምህርታቸውንና የሃይማኖት ዕውቀታቸውን ደረጃ ፤ ወደ ጳጳስ ( Oskof ) ደረጃ ሳይደርሱ አስቀድሞ የሠሯቸውን ልዩ ልዩ ሥራ ዎች ፤ ይልቁንም የቤተ ክህነት ሰዎችና ሕዝቡም እንደምን እን ደሚገምታቸው ለማወቅ እንፈልጋለን ።

፰ ፤ ስለዚህ ነገር የሚመጡልንን መልሶች ካጠናን በኋላ የኢ ትዮጵያንና የቤተ ክርስቲያኗን ጥቅሞች ለመጠበቅ የሚችለውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የሚያሳስበን (አሳብ የሚሰጠን) መሆኑን እና ምናለን ።

፱ ፤ አንዳንዶቹ የቀረቡት ጥያቄዎች ሳያቋርጥ አንድ ሺ ስድ ስት መቶ ዓመት የቈየውን አኗኗርና አኳኋን ለመለወጥ ያመሩ ስለሆኑ በእነዚህ ጥያቄዎች ምክንያት ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ፍራቻችንን እንደብቅዎትም ፤ እግዚአብሔርም በዚሁ ጊዜ ሁሉ (ሺ፮፻ ዘመን) ኢትዮጵያን ጠብቆ አድኗታል ፤ ያለክርክር በነዚህ ባለፉት ዘመናት (ሺ፮፻ ዓመት) የነበሩት ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ካሉት ሰዎች ያነሰ የተማሩና ለኢትዮጵያም ያነሰ የሚያስቡ አል ነበሩም ፤ ደግሞም ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ስለክብርዋና ስለእድገቷ ያለንን ጥልቅ የሆነ ፍቅራችንንና ታላቅ በጎ አድራጎታችንን ግርማዊነትዎ ያውቃል ።

አምላካችን ከፍ ያለውን ሰውነትዎንና ግርማዊት እቴጌን ከን ጉሠ ነገሥታዊ ቤተ ዘመድ ሁሉ ጋራ ጠብቆ እንዲያኖርልንና የታ ላቂቱን ኢትዮጵያ ሕዝብ የተባረኩትን ልጆቻችንን ሁሉ እንዲ ጠብቅልን እንለምናለን ።

www.ethiopianorthodox.org

• ፺ •

ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፤
ለብፁዕ የእስክንድርያ ፓትሪያርክ
በ፲፱ መጋቢት ፲፱፻፵፯ ዓ. ም.
የተጻፈ ደብዳቤ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ።
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለብፁዕነታቸው ሊቀ ጳጳስ ሣልሳዊ መቃርዮስ
የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ፤

ቅዱስ ጸሎትዎና ረድኤትዎ አይለየን እያልን ሰላምታችንን እናቀርባለን ። በመጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. (*) የጻፉልን ደብዳቤ ደርሶናል ። ለኛና ለልጆቻችን ለሰጡን ቡራኬና ለሕዝባችንም ወደ እግዚአብሔር ለሚያቀርቡልን ጸሎት ምስጋናችን እንዲደርስዎ እንወዳለን ።

የላኩልንንም ወረቀት ለሚገባው ለመንፈሳዊ ጉባኤ አስተላልፈንለታልና ፤ ምላሹም በዚያው በኩል ይደርስዎታል ፤ ይኸው የተጀመረው የስምምነት መንፈስ እመልካም ፍጻሜ በፍጥነት እንዲደርስ ምኞታችን ነው ።

መጋቢት ፲፱ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ተጻፈ አዲስ አበባ ከተማ ።

(*) በኢትዮጵያ አቆጣጠር የካቲት ፳፱ ፲፱፻፵፯ ዓ. ም ነው ።

• ፳ •

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ለእስክንድርያ ፓትሪያርክ
የጻፈው መልስ ።

መንፈሳዊ ፣ ጉባዔ ፣ ዘመንግሥተ ፣ ኢትዮጵያ ፣

መጋቢት ፲፰ ቀን ፵፯ ዓ. ም.

የኦርቶዶክሳዊት ፣ ተዋሕዶ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣
ጠቅላይ ፣ ጽሕፈት ፣ ቤት ።

ለብፁዕ አባታችን አቡነ መቃርዮስ ፤
የእስክንድርያ ፓትርያርክ ፤

ቅዱስ ቡራኬዎ ይደርሰን ዘንድ እየለመንን ሰላምችንን በትሕትና እናቀርባለን ።

ባለፈው ሰኔ ፳፩ ፲፱፻፵፮ ዓ. ም. የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ምኞት በ፮ አንቀጾች ገልጸን ጽፈንልዎ ስለነበረ ስለዚሁ ጉዳይ ከሥር ወር በኋላ ወደ ግርማዊነታቸው የላኩትን መልስ አየነው ።

፩) የጠየቅናቸው ዋናዎቹ ጉዳዮች በአንደኛውና በሁለተኛው አንቀጽ ተመልክተው ሳሉ ብፁዕነትዎ ያሰበበት የማያስቸኩለውን አምስተኛውን አንቀጽ ብቻ ይመስላል ፤ ይኸውም በአምስተኛው አንቀጽ ያመለከትንዎ ጥያቄ በጠላት ጊዜ ኢትዮጵያ ከእስክንድርያ ተቋርጣ በነበረችበት ዘመን ክርስቲያኑ ሕዝብ በሃይማኖቱ ጸንቶ እንዲኖር ላደረጉት መነኰሳት ውግዘቱ እንዲፈታላቸው ነው ፤ ውግዘቱ ይፈታላቸው ስንል ወደ ጵጵስና ሥራቸው ይመለሱ ብለን አልጠየቅንም ። ምክንያቱም ወደፊት ጳጳሳት የሚመከከሩበት ጉዳይ በመሆኑ ነው ፤ እስከሁንም ድረስ ከአባ ቁር

www.ethiopianorthodox.org

ሉስ ጋራ ግንኙነት እንዳያደርጉ ከናንተ ወገን በተጠየቅነው መሠረት እንደ ግዞት እንደ ተቀመጡ ናቸው ።

ስለዚህ የጠየቅነው ጥያቄ በጽሕፈት የተላከልዎት ከመላክተኞችዎ ጋራ በሰፊው በቃል ከተነጋገርንና ከገባቸው በኋላ ስለ ሆነ በአራተኛው አንቀጽ በወረቀትዎ ላይ ሐሳባችንን እንዳልተገለጸ አድርገው በመመልከትዎ አዝነናል ፤ ብፁዕ አባታችን ከማንም የበለጠ ለቤተ ክርስቲያናችን ያስባሉ ብለን ስንመኝ በዚህ አስተያየት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ችግር ያልተመለከቱልንና ለነገሩ በቅርብ ቀን መልካም ፍጻሜ ለመስጠት ያልታሰበበት መስሎ ታየን ።

በማንኛውም ረገድ የኛ ጥያቄ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመልካሙም ሆነ በመከራውም ሰዓት ምእመናኖቿን ያለችግር ጠብቃ ከእስክንድርያም ሳትለይ የምትኖርበትን አኳኋን ነው ያመለከትነው ።

፪ )በዚሁ በወረቀትዎ በ፭ኛው አንቀጽ ላይ ስለጠየቁን ጥያቄ የፊተኛውንም ያሁኑንም ወረቀት የጻፍንልዎ በመስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. የቆመው ቅዱስ መንፈሳዊ ጉባኤ ነው ፤ በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. በግንቦት ወር አራቱ መነኰሳት ካይሮ ሄደው የጵጵስና ማዕርግ ተቀብለው የመጡት በዚሁ ጉባኤ መራጭነትና አቅራቢነት ነው ። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ የእስክንድርያ ፓትርያርክ በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስን አዲስ አበባ ላይ አጳጳሰው የሄዱትም በዚሁ ጉባኤ መራጭነትና አቅራቢነት ነው ።

በማናቸውም ረገድ ይህ ቅዱስ ጉባኤ የ፲፪ቱ አውራጃ የአብያተ ክርስቲያናት ወኪሎች ተመርጠው የተሰበሰቡበትና በብፁዕ ዕጨጌው መሪነት እንዲካሄድ በቤተ ክህነታችንና በቤተ መንግሥታችንም የታወቀ ነው ።

፫) ይኸው ቅዱስ ጉባኤ እስካሁን ድረስ በብፁዕነትዎ ወገን የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር የሚያቀልላት ነገር ባለመገኘቱ ምክንያት ፤ ይልቁንም ከሐምሌ ወር ጀምሮ የዲቁናና የቅስና ሥርዓት እንዳይፈጸም ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ተጨቆነች የእስክንድርያው ፓትርያርክ ከነበሩት ከአቡነ ዮሐንስ ጵጵስና የተሾሙት አቡነ



ይስሐቅ ለምእመናኖቻችን የሚገባቸውን ሥራ ሲሠሩ እንዲቆዩ፤ ዲቁናንና ቅስናንም እንዲሰጡ ፈቃዳችን ነውና ብፁዕነትዎ እንዲፈቅድልን እናመለክታለን ።

፬) በወረቀትዎ በ፮ኛው አንቀጽ ለቀረበልን ጥያቄ እገሌ ይሾምልን ብሎ ጉባኤያችን ያቀረበው ስም ለጊዜው የለምና የመንፈሳዊ ዕውቀታቸውንና የችሎታ ደረጃቸውን ለማወቅ ዛሬ አስፈላጊ ጊዜ መስሎ አልታየንም ።

ከዚህ በላይ ጉባኤያችን የገለጠው ሐሳብ ለጥያቄው በቂ ሆኖ ይገኛል ስንል እንመኛለን ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለስምምነት ያለው መልካም መንፈስ ሳይበርድ በከንቱ ጊዜ የሚፈጁትን ጉዳዮች አስወግደው ለዋናው ጥያቄያችን በወረቀትዎ አርእስት እንደ ተመለከተው የመጨረሻው ንግግር የሚደረግበትን መንገድ በቶሎ አስበው እንዲያስታውቁን እናሳስባለን ።

ሰላምታችንን በአክብሮት እያቀረብን ቡራኬዎን ደግመን እንለምናለን ።

ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ

ዘነበረ በመንበረ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ።

www.ethiopianorthodox.org

• ፱ •

## የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄዎች ዋናዎቹን ጉዳዮች አለመቀበሉን ያስረዳበት በ፱ ሰኔ ፲፱፻፷፯ የተጻፈ ።

የኮፕት ኦርቶዶክስ ፓትሪያርክ ግቢ
ከይሮ ።

ከይሮ ፱ኛ ባኡና ፲፮፻፺፩
( ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. )

### ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥያቄዎች ፤ ከቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጠ ትእዛዝ ፤

ቅዳሜት በ፪ ባኡና ፲፮፻፺፩ ( እንደ ኢትዮጵያ ቁጥር በሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ ም ) ደግሞ ሰኞ በ፬ ባኡና ( በ፬ ሰኔ ) በ፫ ሰዓት የእስክንድርያና የኖብያ ፤ የኢትዮጵያ ፤ የቀረውም የመንበረ ቅዱስ ማርቆስ ክፍል ሊቀ ጳጳሳት አባ መቃርዮስ በተቀመጡበት የሲኖዶሱም አባሎች ሁሉ ባሉበት ካይሮ በጳጳሱ ግቢ ሁለት ስብሰባዎች ተደረጉ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበቻቸው ጥያቄዎች ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሊቀ ጳጳሱ በሰኔ ፳፩ ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. ከተጻፈው ከማስረጃ ደብዳቤያቸው ጋር ለታላቁ መንፈሳዊ ጉባኤ ቀረቡ ፤ አባሎቹም በነዚህ ጥያቄዎች ሁለት ዋና ጉዳዮች ተመርኩዞ ተከራከረ ፤ ማለት (፩) ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብቶችና ስለ ሃይማኖት መልክም ሁኔታ ፤ ታላቅ ጥንቃቄ በማድረግ ፤ (፪) ለግብጻውያንና ለኢትዮጵያውያን በሁለቱም ዘንድ በጣም ውድ የሚሆኑባቸውና ከኮብት ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያገናኝዋት ታሪካዊ መተሳሰሪያዎችን በበለጠ ጥብቅ በሆነ ረገድ የሚጠበበቁበት ፤

የተባሉት ማመልከቻዎችና ስለያንዳንዳቸውም የተሰጠ ውሳኔ ከዚህ በታች እንደ ተገለጸው ነው ፤

#### ፩ኛ ፤ ጥ ያ ቄ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳስ ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሾም ጠይቃለች ።



የተቀደሰው ሲኖዶስ የኮፕት ጳጳስ ሲወርድ ሲዋረድ በቈየው ልማድ ለኢትዮጵያ መንግሥት ጳጳስ ሲሾም ማድረግ የሚገባውን ሁሉ በመፈጸም የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግል በ፲፮ መቶ ዘመን ውስጥ ፩፻፲፩ የኮፕት ጳጳሳት እንደ ነበሩበት ጊዜያት ቤተ ክርስቲያንዋ ባንድ ኢትዮጵያዊ ጳጳስ ለመለወጥ አንዳች ያስፈላጊነት ስሜት በማያደርጉበት ረገድ ኢትዮጵያውያን ልጆቿን በልዩ ጨዋነት እንዲጠብቅ ነበር ። ወዲያውም ይህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ያንድ ግብጻዊ (የኮፕት) ጳጳስ መኖር በሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች መካከል የተቀደሰ ኅብረት ምልክት ነው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችም ይህን አንድነት እንዲጠብቅ እስካሁንም በጣም ፈቃደኛ ለመሆናቸው የተቀደሰው ሲኖዶስ ትኒሽም ጥርጣሬ የለው ።

በነዚህ ምክንያቶች ታላቁ የመንፈሳዊ ምክር ቤት (ቅዱስ ሲኖዶስ) አንድ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ እንዲሾም አንዳች አስፈላጊነት ለመኖሩ አይታሰበውም።

#### ፪ኛ ጥያቄ ።

በኋላ በሚጠቀስ ምክንያት ፪ኛና ፫ኛ ጥያቄዎች ከመታየታቸው አስቀድሞ ይህ ፬ኛው ጥያቄ እንዲታይ የሚሻል ሆኖ ለተቀደሰው ሲኖዶስ ይታሰባል ።

በዚህ ባ፬ኛው ማመልከቻ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በካይሮ በተቀደሰው ሲኖዶስ ስብሰባዎች የሚቀመጡ አባሎች ለመላክ እንድትችል ጠይቃለች ።

የተቀደሰው መንፈሳዊ ጉባኤ ይህንን ጥያቄ ፈቅዷል ፤ ስለ ዚሁም እንደ ቤተ ክርስቲያን ሕግጋት በያመቱ የትንሣኤ ሰስተኛ ሳምንት በሚደረገው ስብሰባ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንድትገኝ በመጥራት ቈርጧል ። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ጳጳስና ኤጲስ ቆጶሳት ለስብሰባው ይቀርባሉ ። በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል ስላለው ታላቅ ርቀት የተነሣ በተወሰነው ጊዜ ለመገኘት በሚቻልበት ረገድ ጥሪው ከስብሰባው ቀደም ባለ የሚበቃ ጊዜ ለያንዳንዱ እንዲላክ ያስፈልጋል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ ጥ ያ ቄ ።

**ይህ ፪ኛው ጥያቄ በሁለት ይከፈላል ።**

(፩) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ኤጲስ ቆጶሳትን ለመምረጥና ለምርጫም ለማቅረብ የሚችል አንድ የተለየ ቅዱስ ሲኖዶስ ለራስዋ እንዲኖራት ጠይቃለች ።

ስለዚህ ከዚህ በላይ በ፩ኛው ማመልከቻ እንደ ተጠቀሰው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በካይሮው ቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ውስጥ እንድትገኝ ከፈቀደች ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድ የተለየ ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲኖራት አስፈላጊ እንዳልሆነ ሐሳቡ ነው ። ይልቁንም እነዚህ ሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች ለነገሩም ቢሆን አንድ ቤተ ክርስቲያኖች ናቸው ። በካይሮ ቤተ ክርስቲያን አለቃ መኖሪያ ክፍል ውስጥ የሆነ አንድ ቅዱስ ሲኖዶስ ያላትና ፤ በቅዱሳት ሲኖዶሶችም ሊቀ ጳጳሱ ራሳቸው ፤ ወይም ሊቀ ጳጳስ በማይኖርበት ጊዜያት ተጠባባቂው ካልሆነ በስተቀር በሌላ የማይታይ (ጉባኤ) በመሆኑም ምክንያት ፤ ኢትዮጵያም በቅዱስ ማርቆስ ውስጥ ያንድ የኤጲስ ቆጶስና በታ ብቻ ናት ።

ስለ ኤጲስ ቆጶሳት ምርጫና ማቅረብ ጉዳይ ግን ለዋና ዋና የኢትዮጵያ ገዳማት አለቆች ተለቆ ። የሚመረጡትም ለዚህ ከፍ ላለ ደረጃ የሚገቡ የሚያደርጋቸው ለእውቀትና ለትሩፋት ምግባር አስፈላጊውን ሥያሜ የሚያገኙ መሆናቸው ከተረጋገጡና የብፁዕ ጳጳሱና የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ፈቃድ ከሆነ በኋላ እንዲፈጸም የተቀደሰው ሲኖዶስ ሐሳብ ነው ።

ከዚህ በኋላ ወደ ካይሮ ተልከው እንደቄየው ልማድ ከቅዱስ ሊቀ ጳጳሱ ዘንድ ቀርበው ለሕገኛው የኤጲስ ቆጶስና ክብር የክህነት ቡራኬን ይቀበላሉ ።

(፪) የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያው ጳጳስ ኤጲስ ቆጶሳትን የመሾም (የመባረክ ሥልጣን) መብት እንዲያገኝ ጠየቀች ። ይህን ጥያቄ ቅዱሱ ሲኖዶስ ለመፍቀድ አይችልም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መምህራንም እንደሚያውቁት በግብጻዊ (የኮፕት) ቤተ ክርስቲያንና ተያይዘው በመጡትም ቤተ ክርስቲያኖችም ሁሉ



ሕጎች ይህን በፍጹም የማይፈቅዱ መሆናቸውን መመልከት ነው ። ምክንያቱም የኤጲስ ቆጶስና መባረክ ቅዱሳት ሲኖዶሳት ከሉ ጳጳሳት ጋር በተባበረ በሊቀ ጳጳሳት ሥልጣን ብቻ ነው ። ለጳጳሳት ግን የቤተ ክርስቲያን ድንጋጌዎች ቀሳውስትንና ዲያቆናትን የመክን ሥልጣን ሰጥቷቸዋል ።

ቅዱስ ሲኖዶስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ኑሮ ለማስፋፋት ምኞት ስለአለው አሁን ይህች ቤተ ክርስቲያን ሕዝብዋ የሚጠበቁበት ኤጲስ ቆጶሳት የሚያስፈልጓት መሆንዋን ተገነዘበ ፤ ለጊዜው አራት ኤጲስ ቆጶሳት ለመሾም ቈርጧል ። ይኸውም ለወደፊት እንዳገሩ ስፋት እየታየ ፤ ወይም ሊጨመርበት ወይም እንዲቀነስም ቢሆን ይቻላል ። አንዳዱም ኤጲስ ቆጶስ በጳጳስ ሥር ሆኖ አላፊ የሚሆንበትን የኤጲስ ቆጶስና አገር ክፍል መወሰን ያስፈልጋል ።

## ፫ኛ ፤ ማመልከቻ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ማርቆስ መንበር ለሚቀመጡት ሊቀ ጳጳሳት ምርጫ በሚሆንበት ጊዜ መልክተኞች ለመላክ መብት እንድታገኝ ጠይቃለች ። የኮፕት ሊቀ ጳጳሳት ወዲያውም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት በመሆናቸው ይህ ጥያቄ ደንበኛ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ ይገልጻል ።

ስለ ሊቀጳጳስ ሥያሜና ምርጫ አፈጻጸም አገባብ ባላቸው ባለሥልጣኖች በተፈቀዱት ድርድሮች የተወሰነ ነው ። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በምርጫ ውስጥ የተካፋይነት መብትዋን እንድትሠራበት ትችል ዘንድ የምርጫው ድርድር በሚለወጥበት ( በሚሻሻልበት ) ጊዜ የተባለችው ቤተ ክርስቲያን ጳጳስዋና ኤጲስ ቆጶሳትዋ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም መልእክተኛ ( ወኪል ) እንዲገቡ ሲኖዶሱ ወስኗል ።

## ፬ኛ ፤ ማመልከቻ ።

በ፲፱፻፴፮ ዓ ም (በአውሮፓውያን አቆጣጠር) በኢጣልያን ሕግ መጣስ ጊዚያት ከሕግ በወጣ ረገድ የኤጲስ ቆጶስና ሥራ በተ

www.ethiopianorthodox.org

ቀበሉ ሰዎች ላይ የገዘተውን ግዝት እንዲፈታ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስን ጠይቃለች ።

ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሆኑ አንዳች ወኪሎች ጋር ስለዚህና ስለሌሎች ጥያቄዎች ጭምር የበለጠ ማስረጃ ለመስጠት ግንኙነት ለማድረግ እንዲችል ቢሆን በፈቀደ ነበር ። ስለዚህም እንደ አንድ ምስክር የሚሆን ቅዱስነታቸው ሊቀ ጳጳሱ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንደ አውሮፓ ቍጥር በሐምሌ ፳ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ. ም. በጻፈው ደብዳቤ እነዚህን የተባሉትን ወኪሎች ፤ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እንዲላኩ መጠየቁን ማስታወስ ያሻል ። ዳግመኛም ስለዚሁ ማመልከቻዎች በጭማሪ ማስረጃ በመጠየቅ አንድ ሌላ ደብዳቤ ልከዋል ፤ ነገር ግን ለቅድስናቸው ቅዱስ የመንፈሳዊ ጉባኤ እንዳስረዳው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት አላፊዎቹ ሰዎች ተጽፎ አስቀድሞ በተላኩት ሐሳቦች ደስ የሚያሰኙ ስለ መሆና ቸው አንድ መልስ ደረሰ ።

በዚሁ አኳኋን ቅዱስ ሲኖዶስ የተለወጠበት የለውም ፤ ነገር ግን መጀመሪያ በ፲፱ ባአና ፲፱፻፹፱ (በኢትዮጵያ ቍጥር ሰኔ ፲፱ ፲፱፻፹፩) ለጥቆ እንደተመለከተው በወሰነው ከነዚያ ግዝት እንዲፈታላቸው ከተጠ የቀላቸው ሰዎች ጋራ ለመነጋገርና ለመቁረጥ ነው ሐሳቡ ።

« አግባብ ከሌላቸው ባለሥልጣኖች ልዩ ልዩ የጽሕፈት ደረጃ ዎች ተቀበሉ የተባሉት ኤጲስ ቆጶሳትና የሌሎችም ግዝት ስለመፈ ታት እያንዳንዱ ከክህነት መስጠት በፊት ከጥንት ነገሩ የሚመለሱ እንዲሆኑ ያሻል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስለ አቡነ ይስሐቅ ግዝት መፈታት ጥያቄ አቀረበች ፤ እሳቸው የተገዘቱበት ምክንያት የኤጲስ ቆጶስና ክህነት ሲቀበሉ የገቡትን ቃል ስላፈረሱ ነው ። እንደውሳኔው ቃላቸ ውን ቢያፈርሱ ሊገዘቱና ለመገዘትም የተገቡ መሆናቸውን አስቀ ድመው ፈርመው አረጋግጠዋል ። ነገር ግን ብፁዕ ጳጳሱና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፤ ቅዱስ ሊቀ ጳጳሱ ይቅርታ እንዲያደርጉ ጠየቋ ቸው ፤ በዚያኑ ጊዜ ብፁዕ አባ ጢሞቴዎስ ወደ አዲስ አበባ በ፲፱ ፻፺፩ ( በ፲፱፻፹፫ ዓ ም ) በበጋ ወራት የተላከው የከንት መልእክት ፕሬዚዳን ፤ አባ ይስሐቅ ቅዱስ ሲኖዶስ በቈረጠው መፈጸማቸውንና የቤተ ክርስቲያንንም ሥራዎች ማቋረጣቸውን መሰከሩ ።



ቅዱስ ሲኖዶስም በቤተ ክህነት ሥነ ሥርዓት መሠረት በእሳ ቸው ላይ ቅጣት የመጣል ፈቃዱን በመግለጽ ላይ ሳለ ከአባ ሎች ውስጥ ከዚህ ቅጣት ቅድስናቸው ሊቀ ጳጳሱ ምሕረት እን ዲያደርጉ በትሕትና ለመኑ ። በዚሁ ቅዱስ ሲኖዶስ አባ ይስሐቅን ከግዝቱ ለመፍታት ቈረጡ ። ይቅርታም አደረጉላቸው ፤ ከማናቸ ውም ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ቅጣት ሁሉ ነጻ አወጣቸው ። ይህም ሲሆን በኤጲስ ቆጶስና ሥራቸው እንዲገቡ በሱውም እንዲረጉ የቤተ ክርስቲያንንም አገልግሎቶች እንዲፈጽሙበት እንደ ቤተ ክር ስቲያንም ሕግጋት ወደ ሌላ አንዳች ኤጲስ ቆጶስና እንዳይሄዱ ላለቃ ቸው ለብፁዕ ጳጳሱም እንዲታዘዙ እያስረዳ ነው ።

## ፮ኛ ጥያቄ ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፤ ፩/. ሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች የሚተሳሰሩባቸው የመነኰሳት ሚሲዮኖች ስለማግኘት ፣ ፪/ በኢት ዮጵያ ውስጥ አንድ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ስለማቆም ጠይ ቃለች ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ( ታላቁ የግብጽ መንፈሳዊ ምክር ቤት ) እነዚህ ሁለቱ ጥያቄዎች የሚገቡና በሙሉም የሚፈቀዱ መሆና ቸውን ገልጾ ላፈጻጸማቸውም ስለሚያስፈልጉ ጉዳዮች ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከመማከር በኋላ እንዲፈጸሙ ይሆናሉ ሲል ያስ ረዳል ።

ከዚህ በላይ የተመለከቱት በቅዱስ ሲኖዶስ የተቈረጡ ናቸው ።

| | |
|---|---|
| የቅዱስ ሲኖዶስ | የቅዱስ ሲኖዶስ ፕሬዚደንት ፣ |
| ዋና ጸሐፊ | ( ማኅተም ) |
| ቶማስ | መቃርዮስ ፫ኛ |
| የበሬኸረና ጋርቢያ ጳጳስ ። | የቅ ማ መ ሊቀ ጳጳሳት ። |

www.ethiopianorthodox.org

. ፲ .

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ ፤ ከኮፕት ጉባኤ በ፱ ሰኔ ፲፱፻፵፯ የተጻፈለትን ቃል ተመልክቶ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ያቀረበው የውሳኔ ማስታወቂያ ።

በኢትዮጵያና በግብጽ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ስለ ሊቀ ጵጵስና ሹመት ጉዳይ ፤ ብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ዋና ሰብሳቢ ሆነው በተቀመጡበት ፤ ዛሬ ሐምሌ ፮ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ.ም. ዓርብ በ፬ ሰዓት በተቀደሰው መንፈሳዊ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ስብሰባ ተደረገ ።

በጉባኤው የነበሩት ከዚህ በታች የተጻፉት የመንፈሳዊ ጉባኤ መደበኞቹ አማካሪዎች ናቸው ።

፩ ፤ ሊቀ ሊቃውንት ገብረ መስቀል ፣
የታዕካ ነገሥት ገዳም መምህርና ቆሞስ

፪ ፤ መምህር መልዕክቱ ።
የመካነ ሥላሴ ገዳም መምህርና ቆሞስ

፫ ፤ መምህር ራስ ወርቅ ።
የአራር ባይኔ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም መምህርና የመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ሹም ።

፬ ፤ አለቃ ልሳነ ወርቅ ።
የየካ ሚካኤል ደብር አለቃና የመንፈሳዊ ጉዳይ ዳኛ

፭ ፤ መምህር ወልደ ሚካኤል ።
የሐርያት ቤተ ክርስቲያን መምህርና ቆሞስ

፮ ፤ አለቃ መኰሪያ አብዩ ሆይ ።
የቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ደብር አለቃ

፯ ፤ አጋፋሪ ዘወልዴ ።
የገነተ ጊዮርጊስ ደብር ካህን

፰ ፤ ሊቀ ጠበብት ወቤ ።
የዑራኤል ደብር ካህንና ፤ ሊቀ ጠበብት ።

፱/ መልአከ ሰላም የውነቱ ፤
የደንበጫ ሚካኤል ደብር አለቃና የጎጃም አውራጃ አብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ ፤



፲፡ መርጌታ ገሡ ፤
የአክሱም ገዳም መርጌታና ፤ የትግሬ አውራጃ አብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ ፤ (፩ኛ)

፲፩፡ አለቃ ወልደ ማርቆስ
በመቀሌ የመንፈሳዊ ጉባኤ አማካሪና ፤ የትግሬ አውራጃ አብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ ፤ (፪ኛ)

፲፪፡ አለቃ ሐዋዝ
በሐረር የመካነ ሥላሴ ደብር ካህንና የሐረር አውራጃ አብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ

፲፫፡ መምሬ በሼ
የኢሉባቦር አውራጃ አብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ

፲፬፡ አባ በላይ
የወለጋ አውራጃአብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ

፲፭፡ አለቃ ዓለሙ ደርሰ
የወሎ አውራጃ አብያተ ክርስቲያናት መልከተኛ

እነዚህ የመንፈሳዊ ጉባኤ አባሎች (ቆሞሳትና ፤ መምህራን ፤ ሊቃውንትና ካህናት) በተሰበሰቡበት ፤ የኮፕት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ካይሮ ላይ በ፱ ባአና ፲፰፻፹፩ ዓመተ ሰማዕታት ፤ እንደ ኢትዮጵያም አቆጣጠር በሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ትእዛዝ ብሎ የጻፈው መልዕክት ተነበበ ።

ይኸውም መልክት ፤ ከኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ በሰኔ ፲፬ ቀን ፲፱፻፵፯ ዓ. ም. ተጽፈው ከነበሩት ጥያቄዎች ፤ ዓይነተኛውን ጕዳይ የሚቃወምና ሁለቱ ቤተ ክርስቲያኖች ወደ ስምምነት እንዳይደርሱ አድርጎ የሚከለክል ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፤ አስተዳዳሪዋ የሚሆነውን ሊቀ ጳጳሳት በቋንቋዋ ከሚሰብኩላትና በመከራዋ ጊዜ ከማይለዩዋት ፤ ተወላጆቿ ከሆኑ ከመንፈሳውያን አባቶች መካከል መርጣ እንድታቀርብና የእስክንድርያው ፓትርያርክ ባርኮ እንዲሾምላት ፤ ሊቀ ጳጳሳትዋም ሌሎቹን ጳጳሳት ከበታቹ ለመሾም መብት ያለው እንዲሆን ስትል ጠየቀች ። የኮፕት ጉባኤ ግን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስነት ለግብጻዊ ብቻ እንዲሆን ፈለገች ። ከቶውንም ይህ አሳብዋ

www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ እንደ ተወደደ አስመስላ ፣ እውነት ነው የሚለው ላይኖር አስታወቀች ።

የተቀደሰው የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀበለው የማይሆንለት ከኮፕት ጉባኤ የመጣው ይህ ውሳኔ ፣ ለቤተ ክርስቲያን መሠረት የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የክርስትናን መንፈስ የሚቃወም መሆኑ ፣ በጉባኤው ተመርምሮ ታወቀ ። የክርስትና መንፈስ የወገንና የዘር ልዩነት አያደርግም ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «አይሁዳዊ ወይም ዕርዕ ፣ ባርያ ወይም ነፃ የለም ፣ ሁሉም በክርስቶስ አንድ ናቸው » ብሎ ተናግሮአል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በመልክም ትሕትና ያቀረበቻቸው ዋነኞች ጥያቄዎች የኮፕት ጉባኤ ገፍታ መጣልዋን ከተረዱት በኋላ ፣ ከላይ የተጠሩት የጉባኤው አባሎች የሚከተለውን ውሳኔ አወጡ ።

፭ ፤ በጠላት ወራሪነት ዘመን አቡነ ቄርሎስ ከጠላት ባለሥልጣኖች ጋር ተስማምተው ብዙ ወራቶች ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን በታች ናትና በጠቅላላው ያስተዳድሩ መብት እንዲሰጠኝ ሲሉ ያቀረቡት ሐሳብ እዚህ አዲስ አበባ ላይ የማይፈጸምላቸው ቢሆን ይህንኑ አስፈጽማለሁ ብለው ለጉባኤው ሳይገልጹ ፣ በሊቀ ጳጳስነቱ ሥራ አቡነ አብርሃምን ወክለው በፈቃዳቸው ወደ ኢጣሊያ አገር ሄዱ ። በዚያም አሳባቸው የማይፈጸምላቸው ቢሆን ወደ ግብጽ ገብተው ስለቀሩ ቤተ ክርስቲያናችንን ከመዘጋቱ በኋላ ይልቁንም ልዩ ልዩ የሆነ የባዕድ ሃይማኖት እየተስፋፋ የተዋሀዶ ሃይማኖት እየደከመ የሚሔድ ቢሆን በጊዜው ካሉት ባለሥልጣኖች አስፈቅደን ሃይማኖታችንን ለመጠበቅና የቤተ ክርቲያናችንን ችግር ለማቅለል ስንል በተደነገገ በመንፈሳዊ ሥርዓት መክረን ሊቀ ጳጳስና ጳጳሳት ሾምን ።

ይኸው አፈጻጸም ለሃይማኖታችንና ለቤተ ክርስቲያናችን መልካም አጠባበቅ ከመስጠት ጋራ ምዕመናኑን በሚገባ እያጽናና የጠላትን ዘመን በኅድዓት እንዲያሳልፍ የተደረገ ነው እንጂ ከቅዱስ ማርቆስ አባትነት ለመለየት የተደረገ አይደለም ። ወደፊትም ቢሆን



ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈሳዊ አስተዳደርዋ ራስዋን ችላ ከመኖርዋ በቀር በሃይማኖት ከቅዱስ ማርቆስ አባትነት የሚለያት የለም ። . . .

፮ ፤ የኮፕት ጉባኤ ፣ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የቀረቡለትን የትሕትና ጥያቄዎች በመቀበልና የሚገባትን ክብር በመስጠት ፈንታ እንደዚሁ ያለ መልስ መጻፉ የሚያሳዝን ነው ። በዚህም አስተያየት ኮፕቶች የኢትዮጵያን ልጅነት እንዳልፈለጉ አረጋግጠዋል ሊባል የሚቻል ነው ።

እንግዲህ እነሱ አባት ለመሆን ሳይፈልጉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የግብጽ ልጅ ልሁን እያለች ልትሽቈጠቈጥ የሚገባት አይደለም ። ወደፊትም የቅዱስ ማርቆስ አባትነት ሳይቀር ፣ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን ለመሾም ሥልጣን ያለው ኢትዮጵያዊ ሊቀ ጳጳሳት ፣ ከኢትዮጵያ መንፈሳውያን አባቶች መካከል በሊቃውንት ሲኖዶስ ተመርጦ እንደ መጽሐፍ ሥርዓት ይሾማል እንጂ እንግዲህ ወደ ግብጽ የምንሄድበት ጉዳይ የለም ። በዚህም ሁሉ ምክንያት ከዛሬ ጀምሮ ከግብጽ (ኮፕት) ጋራ የተለየን ሆነናል ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ የወሰነው ይህ ውሳኔ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ቀርቦ ፍጻሜ ያገኝ ዘንድ ጉባኤው ለብፁዕ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ያሳስባል ። . . .

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org